# ትግሉን ከተገዳጅነት ወደ አስገዳጅነት እናሸጋግረው ማለት ጦርነት ማወጅ ሊሆን፡አይችልም!

አቶ አንዳርጋቸውና አቶ እምነቱን (በጋራ) የጻፉትንና ለውይይት መነሻ እንዲሆን ያቀረቡትን ጥናታዊ ጽሁፍ በጥሞና አንብቢያለሁ። ጽሁፉ "ከትናት ተምሮ ፤ ዛሬ ሞክሮ፤ ለነገም መክሮ ማደር" የሚለውን ብችኛ የስኬት ጎዳና መርህ የተከተለ:- ጥልቅና ጊዜ ተወስዶና ጥናት ተደርጎበት የተሠራ ሥራ ለመሆኑ የጽሁፉ ይዘት መስካሪ ነው። ለዚህም ሥራቸው ጸሃፊዎቹን ላመሰገን እወዳለሁ።

ከላይ እንዳልኩት በ23 ገጾች የተከሸነው ይህን ጥልቅ ጥናታዊ ጽሁፍ ለመረዳት ትንሽ ግዜ ወስዶ በጽሞና ማንበብ የሚያስፈልግ ይመስለኛል።(የመረዳት ችሎታችን ያንዱ ካንዱ ሊለያይ ቢችልም ሁሉም እንደ አቅሙ ...ማለቴ ነው)። ይህን ለማለት ያስገደደኝ ጽሁፉ ለውይይት የቀረበ እንጂ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣ ተፈጻሚነቱም በጠመንጃ አንጋች ኃይል የሚረጋገጥ አዋጅ አለመሆኑን በመዘንጋት የተሰጡ አስተያየቶችን እዚህም እዛም ለማየት በመቻሌ ነው። ከዚህም ባሻገር ጽሁፍ ጦርነትን እንዳወጀ ተደርጎ የሚሰጠው የተቃውሞ አስተያየት ለኔ ለዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በጣም ግራ የሚያጋባ ሆኖብኛል። በኔ ንባብ ጽሁፉ የትጥቅ ትግል ብቸኛው አማራጭ መሆኑን አስረግጦ ያስቀመጠበትን ክፍል ለማየት አልቻልኩም፡፤ አመጽ ማለት ጦርነት ማለት ነው የሚል ትርጓሜ ተሰጥቶት ከሆነ የኔ ችግር ወይም ጦርነት ታወጀ ባዮቹ ችግር የሚጫረው እዚህ ጋ ነው ማለት ነው።

እንደሚመስለኝ ይህ አወዛጋቢ ትርጓሜ በጽሁፉ ላይ የሚደረገውን ውይይት አቅጣጫ የሚያስት ይመስለኛል። ስለሆነም በዚህች ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኮረ አጭር መግለጫ ከጸሃፊዎቹ ብናገኝ ለቀጣዩ ውይይት ስምረት ትልቅ እረዳት ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ቢያንስ ቢያንስ አቶ አንዳርጋቸው በጽፋቸው ጦርነት አውጀዋል የሚሉ ወገኖችና እኔ አንድ አይነት ጽሁፍ አንብበን ነገር ግን ሁለት አይነት ግንዛቤ ይዘናልና ችግር አለ ማለት ነው። ስለዚህ ይህን የግንዛቤ ልዩነት ወደ አንድ አቅጣጫ ለማምጣት ተጨማሪ ማብራሪያ ማስፈልጉ ትክክል ነው ባይ ነኝ። ለውይይት መነሻ በሆነ አንድ ጽሁፉ ላይ አንድ አይነት ግንዛቤ በሌለበት ሁኔታ የሚቀጥል ውይይት ከቶውንም መደማመጥና መረዳዳት ሊኖረው አይችልም።

ይህን ካልኩኝ በኋላ የአቶ አንዳርጋቸውና የአቶ በእምነቱ ጽሁፍ ለኔ ከሰጠኝ ግንዛቤ በመነሳት አስ ተያየቴን ላቅርብ።

በኔ እምነት ጽሁፉ በዋናነት ያንቀረዘዘው መልእክት ወይም ሊያቀብለን የሚሻው ጭብጥ ከትናትናው የትግል ተመክሯችን በመነሳት ዛሬ የምንገኝበት መርምረን የነገውን ደግሞ ልንመክር የሚገባን የታሪክ ምዕራፍ ላይ እንደምንገኝ ነው። ጽሁፉ ይህን እንደ አጠቃላይ ማሳሰቢያ አስቀምጦም በመነሻነት የትናቱን የትግል ጎዳና ጉዞ ድክመትና ጥንካሬ ገምግሞ ዛሬ የምንገኝበት አጣብቂኝ ሁኔታም ቃኝቶ አገናዝቦ የነገው አካሄዳችን እንደትናቱም እንደዛሬውም መቀጠል የለበትም የሚል ደምዳሜ ላይ የደረሰ ጽሁፍ ነው። እስካሁን የተጓዝነበት መንገድ የማያዋጣ ስለመሆኑ በዚህ ጽሁፍ ላይ የተንጸባረቀው፦ ከአለም ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታና ከሁሉም በላይ ደግሞ ከወያኔ ድርጅታዊ ባህሪ በመነሳት የቀረበው ግምጋሜ ከበቂ በላይ ነው እላለሁ። እዚህ ድረስ ማንም ምንም ተቀውሞ ሊያነሳ የሚችልበት ምክንያት አይታየኝም፡፡

የሃሳብ ልዩነቶቹ የሚፈጠሩት ነገ የምንጓዝበትን መንገድ በመምረጡ ረገድ ይመስለኛል። ነገ የምንጓዝበትን መንገድ በመምረጥ ረገድ የአቶ አንዳርጋቸውና የአቶ በእምነቱ ጽሁፍ እንደሚለው በምርጫ 97 የቅንጅት እንቅስቃሴና ውጤት የደነበረው ወያኔ ያንን መሰል አደገኛ አጣብቂኝ ውስጥ ላለመግባት በጭላንጭልም ቢሆን ፈንጥቀው የነበሩትን የዲሞክራሲ መብቶችና አሰራሮች እየተከታተለ በመድፈን ላይ በሚገኝበት ሁኔታ ሰላማዊ ትግል የትም ሊያደርስ አይችልም ነው።

እንግዲህ በዚህ ጸሃፊ እምነት የሃሳብ ልዩነቱ የተጫረው በዚህች ነጥብ ላይ ነው። አቶ አንዳርጋቸውና ባልደረባቸው ሰላማዊ ትግል አያዋጣም ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? የሚለው ጥያቄ ለጽሁፉ አቅራቢዎች እያቀበልኩ ከጽሁፉ አጠቃላይ ይዘት በመነሳት የራሴን ግንዛቤ በተጓዳኝ ላቅርብ።

ሠላማዊ ትግል አያዋጣም ሲባል የቱን አይነት ሰላማዊ ትግል ነው የማያወጣው? በሚል ሊነሳ የሚችል ጥያቄ እንደሚኖር መገመት ከባድ አይሆንም። ለዚህ ጥያቄ ደግሞ ስንት አይነት ሠላማዊ ትግል አለ? በሚል ጥያቄን በጥያቄ የሚያጠናፍር ምላሻ ልንሰጠው እንችል ይሆናል። ይሁን እንጂ ይህን ማድረጋችን ጥቅም የሌለው የመደናቆርና አላስፈላጊ እሰጥ አገባ ውስጥ ከማሰገባቱ በስተቀር አቅጣጫ ፍለጋ ለምናደርገው ጥረት ምንም አይፈይድምና በሰላማዊ ትግል ትርጓሜ ዙሪያ ያለንን ግንዛቤ ልንመለከተው ግድ ይለናል። ።

ሠላማዊ ትግል አያዋጣም ሲባል የቱን አይነት ሰላማዊ ትግል ነው የማያወጣው?

በኔ ግንዛቤ አቶ አንዳርጋቸው ከእንግዲህ የሰላማዊ ትግል አያዋጣም ሲሉ ፦

- የወያኔን መንግስት ይሁኔታ(ፈቃድ) እየተጠበቀ የሚደረግ የሰላማዊ ትግል አያዋጣም ማለታቸው ነው።
- ከአገዛዙ ተጽእኖ ነጻ የሆኑ የዲሞክራሲ ተቋማት በሌሉበት ሁኔታ፤ የሰላማዊ ትግል አያዋጣም ማለታቸው ነው።
- የመንግስትን በመንግስትነት የመቆየት አላማ ለማስፈጸም የተደነገጉ ህግጋቶችን እንደ እንደ ህገ-መንግስት ተቀብሎና አክብሮ የሚደረግ ሰላማዊ ትግል አያዋጣም ማለታቸው ነው።
- ሥማችሁ አላማረኝም! ስም ቀይሩ፦ ሲባል እሺ! ስብሰባ የምታደርጉት እኔ ስፈቅድ ነው ሲባል ይሁን! እየተባለ የሚደረግ የሰላማዊ ትግል አገዛዙን የዲሞክራሲያዊ መንግስትነት ጭንብል ለማልበስ ካልሆነ በስተቀር ለሕዝብ መብት መከበር የሚፈይደው ነገር የለም ማለታቸው ነው።ይህ ደግሞ ማንም አሌ የማይለው እውነት ነው።

በመሰረቱ እዚህ ላይ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ቅንጅት በቅርቡ ስሙ ሲነጠቅ አሜን ብሎ ስሙን ለውጦ ለመታገል መወሰኑን የተቀበለነው የስም ለውጡ በድርጅቱ ሕልውና ላይ የሚያደርሰው አሉታዊ አንድምታ አለመኖሩ በመገንዘብ እንጂ ድርጅቱ ወደፊትም የወያኔ ህግጋትና ኢ-ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎችን ሁሉ በዚሁ መልክ አሜን ብሎ እየተቀበለ በመጓዝ ከውጤት ይደርሳል የሚል ቅንጣት ታክል እምነት ኖሮን አለመሆኑ ነው፡፤

በኔ ግንዛቤ አቶ አንዳርጋቸው ለሰላማዊ ትግል ቅድመ ሁኔታዎች ያስፈልጋሉ ያሉንም፦

- ነጻ ፍርድ ቤት ፤ ነጻ ሚዲያ፤ ከመንግስት ተፅዕኖ የተላቀቀ የምርጫ ኮምሽንና....ለህገ-መንግስቱ ተገዢ የሚሆኑ የፖሊስና የመከላከያ ኃይላት በሌሉበት ሁኔታ እስካሁን እንደተጓዝነው አይነት የሰላማዊ ትግል ስልት አያዋጣም ማለታቸው ነው፡፤ ይህም ደግሞ በተግባር ያየነው ነባራዊ ሃቅ እንጂ በአቶ አንዳርጋቸው ጽሁፍ ላይ የከተመ መላ ምት አይደለም። ከዚህ ጭብጥ ተነስተን ስንመረምረው የወያኔን በጎ ፈቃድ እየጠበቁ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አያዋጡም መባሉ ትክክል አይደለም የሚል ከወያኔ በስተቀር ሊኖር አይችልም ባይ ነኝ።

ይህ ከሆነ በቀጣይ ምን አይነት የትግል ስልት እንከተል በሚለው ምሶሶ ጉዳይ ዙሪያ የአቶ አንዳርጋቸው ጽሁፍ ያስቀመጠውን እንመልከት፦አሁንም ለኔ እስከገባኝ በአጭሩ ሕዝባዊ እንቢታ (civil disobedience) የታከለበት የወያኔን መንግስት አስገድዶ የሕዝብን መብት እንዲያከብር የሚያደርግ የትግል ስልት እንከተል የሚል ነው፡፤ በኔ እምነት ይህም ቢሆን ሌላው የሰላማዊ ትግል ስልት ነው፡፤ ሕዝብ ጠመንጃ አንስቶ ጎራ ለይቶ እስካልተዋጋ ድረስ አይነቱና ደረጃው ይለያይ እንጂ ሁሉም የሥሰላማዊ ትግል አካል ነው። አያዋጣንም ይቅር የምንለውና ያዋጣናል እንጓዝበት በምንላቸው የሰላማዊ ትግል ስልቶች መካከል ያለው ልዩነት በመንግስት የመገደድና መንግስትን በማስገደድ መካከል ያሉ ልዩነቶች ናቸው።

በመሰረቱ አመጽ የሚለውን ቃል ከጠመንጃና ከጥይት ጋር በቅጽፈት የምንጋናኝበት ምክንያት ለምን እንደሆነ አይገባኝም ። አመጽ በዝምታም ይከናወናል፡፤ እኔም ለአቶ አንዳርጋቸው ላነሳ የምሻው ጥያቄ ይህ በሰፊው ያብራሩትን አመጽን አማክሎ የሚንቀሳቀስ የትግል ስልት የሰላማዊ ትግል ሌላው መልክ መሆኑን ለመግለጽ ለምን እንደተቸገሩ ነው። ይህን ጥያቄ አቀብዬ አሁንም ወደራሴ አስተያየት ስመለስ፦ አቶ አንዳርጋቸው በጽሁፋቸው ላይ ምናልባት ይህ ሕዝባዊ እንቢታን ያሚያማክለውን የትግል ስልት ሌላው የሰላማዊ የትግል ስልት መሆኑን የገለጹበት አጋጣሚ ያለመኖሩና በሕዝባዊ አመጽነታቸው ዋቢ አድርገው የጠቃቀሷቸው የሌሎች አገሮች ተመክሮዎች የቃሉን ትርጓሜ ወደ ጦርነት እንዲያዘንበል ዳርጎት ካልሆነ በስተቀር በኔ እምነት ሕዝባዊ አመጽም ሠላማዊ ትግል ነውና ሰላማዊ ትግል አብቅቶለታል የሚለው ሃረግ ይህን የትግል ስልት አያጠቃልልም እላለሁ።

የአቶ አንዳርጋቸውና የአቶ በእምነቱ ጽሁፍ ፦ ዲሞክራሲያዊ ትግሉን ወደፊት ለማራመድ ምን መደረግ አለበት? በሚለው ጥያቄ ሥር ከተራ ቁጥር 1- 5 ያስቀመጣቸውን ነጥቦች ብንመለከት

1-ትግሉ ያጎናጸፈንን ድል በጽኑ መሰረት ላይ ማቆም
2-የተጋለጡትን የወያኔ ድክመቶች ተመልሰው እንዳይሸፈኑ ማድረግ
3-የቀረውን የወያኔ ደካማ ጐች ማወላለቅ
4-የትግሉን ድክመቶች ማረቅ
5-ይህን ለማድርግ ትክክለኛ የትግል አቅጣጫ መምረጥ የሚሉ ናቸው

እንግዲ መሰረታዊ ያሏቸውን እነዚህን 5 ተግባራት ለማከናወን ያስችላሉ ብለው በዝርዝር ያመላከቷቸው የትግል ስልቶች በሙሉ ሰላማዊ የትግል፡ስልቶች፡ናቸው።ነገር ግን የመንግስትን አስገዳጅነት አሜን ብሎ በማይቀበል ህዝባዊ እንቢታን ያማከል ጠንካራ የሰላማዊ ትግል ስልቶች ናቸው።ከዚህ፡ውጭ አንድም፡ቦታ ቢሆን በጠመንጃ አፈሙዝ ሊከወኑ ይገባቸዋል ያሉበት አጋጣሚ የለም። ሊተገበሩ ይገባቸዋል ብለው የዘረዘሯቸውን 5 ነጥቦች ይዘት በቁማቸው እንኳ ብንመለከት በነቃና በተደራጀ የፖለቲካ ወይ ሕዝባዊ ሃይል እንቅስቃሴ የሚከወኑ እንጂ ከክፍለ ጦርና ከብርጌደ ጋር የሚያገናኛቸው ነጥብ ማግኘት አይቻልም።ስለዚህ አቶ አንዳርጋቸው የነገሩን የሰላማዊ ትግሉን ማርሽ እንድንቀይር እንጂ ከሃዲዱ እንውጣ ብለው አይመስለኝም።

ሌላው ቀላሉ ማገንዛቢያ (Simple Logic) ደግሞ አቶ አንዳርጋቸው ከትጥቅ ትግል በበለጠ ሰላማዊ ትግል ከፍተኛ መስዋእትነትና ድፍረትን እንደሚጠይቅ ለማሳየት “ **...ለፍርሃት ከሆነ ጠመንጃ አንስተን ብንዋጋ ይሻላል**” የሚለውን የጋንዲን ታሪካዊ ብሂል ዋቢ አድርገው ከነገሩን በኋላ እኛንም እንደ ፈሪ ወደ ጦርነት እንሂድ ይሉናል ብሎ ማሰብ እንደማይቻል ነው። አቶ አንዳርጋቸው ያሉን ሰላማዊ ትግሉን ከተገዳጅነት ወደ አስገዳጅነት እናሸጋግረው ነው፡፤ በአጭሩ።

የተሳሳተ ግንዛቤ ወስጄ ከሆነ ጸሃፊዎቹ ወደፊት ከሚሰጡት ማብራሪያ እርምት፡ ልወስድ፡ እችላለሁ። ለግዜው ግን ለኔ የገባኝ ይህ እውነታ መሆኑንና እውነታውንም ደግሞ እንደምደግፈው ለመግለጽ እፈልጋለሁ።

**አዜብ ጌታቸው**
From Down Under